# ለሴቶች ግርዛት: ስለአከፋፈት አሠራር መረጃ

the women's
the royal women's hospital
victoria australia

**ተገርዘው ከነበረ እንደገና ማስከፈት ሊያስፈልግዎ ይችላል:**

- ከማርገዝዎት በፊት, ወይም
- አርግዘው እያለ, ወይም
- በሚወልዱበት ጊዜ, ወይም
- በሕይወት ሲኖሩ በሌላ ጊዜ ይሆናል።

በአሁን ጊዜ ነብሰጡር ከሆኑ ከ20 እስከ 30 ሳምንታት ባለው ጊዜ ውስጥ ወይም በሚወልዱበት ጊዜ ህጻኑ እንዲወጣ መንገድ ይሆን ዘንድ ማስከፈት ይችላሉ።

በአውስትራሊያ ከወለዱ በኃላ እንደገና መሰፋት ህጋዊ አይደለም። ታዲያ እርስዎን ከሚንከባከቡት ሐኪም፣ አዋላጅ ወይም ከአፍሪካ ሴቶች ሠራተኛ (FARREP) ጋር መወያየት አለብዎት።

ስለ አሠራሩና ቀዶ ጥገናው ከሐኪም ጋር ለመወያየት ጊዜ ሊወስድ ሲችል፣ ታዲያ በተቻለ ፍጥነት ስለዚህ ጉዳይ ለሐኪምዎ ወይም ለአዋላጅ መናገር ይሆናል።

ይህ የአንድ ቀን ቀዶ ጥገና አሠራር በሆስፒታል ውስጥ ሲካሄድ እንዲሁም ለተደረገው ግርዛት ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ  አጠቃላይ የሆነ ማደንዘዣ/ anesthesia መድሃኒት ይደረጋል። ታዲያ የቀዶ ጥገናው በሚያልቅበት ጊዜ በዚያውኑ ቀን ወደ ቤትዎ መሄድ ይችላሉ።

ቁስሉን ለመንከባከብ ሲባል የሀፍረተ ስጋን አካባቢ ማጽዳት ያካትታል እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የሕመም ማስታገሻ መጠቀም ነው። በአብዛኛው እስኪድኑ ድረስ ከ2 እስከ 3 ቀናት በቤትዎ እርፍት ማድረግ ይሆናል።

**የሰውነት ለውጦች የሚያካትተው:**

- ሽንት መሽናቱ መፍጠን፣ ከባድና ድምጽ ይኖረዋል
- ፈጥኖ የወር አበባ መፍሰስ፣ ከበድ ያለና የጠነከር ሲሆን አነስተኛ ሕመምና የደም መርጋት ይኖረዋል
- የመግቢያ ቀዳዳው ሰፋ ስለሚል በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ህመሙ ቀለል ያለና የተዳከመ ስሜት እንዲኖር ያደርጋል

**ከቀዶ ጥገናው በኃላ ድጋፍ:**

ስለምናቀርበው አገልግሎት ማለት ትራንስፖርት፣ የሕጻን እንክብካቤ፣ አስተርጓሚና እስኪያገግሙ ድረስ በቤትዎ መርዳት ስለምንችል የቀዶ ጥገናው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለሠራተኞች መጠየቅ ይቻላል።

**ስልግርዛት በሚመለከት ለመነጋገር ቀጠሮ ለማቀናጀት ከፈለጉ:**

ነብሰጡር ከሆኑና በሮያል የሴቶች ሆስፒታል በሐኪም ወይም በአዋላጅ ነርስ የሚታዩ ከሆነ በሚቀጥለው ቀጠሮ ሊያነጋግርውቸው ይችላሉ።

ነብሰጡር ካልሆኑ ለተመላላሽ ታካሚ መደወል ሲችሉ ለነርስ/አዋላጅ በስልክ 9344 2183 ደውሎ ማነጋገር ይቻላል።

**በበለጠ ማብራሪያ ካስፈለግዎት ከዚህ ከሚከተለው አንዱን መጠየቅ:**

Outpatient midwife – 9344 2183

African Women's worker (FARREP) – 9344 2211

Women's Health Information Centre – 9344 2007

በአካባቢዎ ላለ ሐኪም (GP)